ሰመጉ
HRCO
# የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ
# HUMAN RIGHTS COUNCIL

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው።
HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

ጳጉሜ 04 ቀን 2009 ዓ.ም.

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## በግብር ጭማሪው ላይ ቅሬታና ተቃውሞ ለሚያሰሙ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት የሚሰጠው መንግሥታዊ ምላሽና የጉዳዩ አያያዝ ሰብዓዊና የዜግነት መብቶቻቸውን የጠበቀ ሊሆን ይገባል፤

-------

## በክልሎች መካከል ለግጭት መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች በአስቸኳይ እልባት ይሰጣቸው

## 1. በንግድ ማህበረሰቡ ላይ የገቢ ግምትና የግብር አተማመንን ተከትሎ በነጋዴዎች የተነሱ ቅሬታዎችና ተቃውሞ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 41/1 ማንኛውም ዜጋ በመረጠው የስራ ዘርፍ የመሰማራት መብት እንዳለው ይደነግጋል። ይህንን የዜጎችን መብት የማሟላት ግንባር ቀደም ሃላፊነት የተጣለው በመንግስት ላይ ነው። መንግስት የሚያወጣቸው ህጎችና መመሪያዎች እንዲሁም የሚወስዳቸው እርምጃዎች የዜጎችን ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ ያገናዘቡና የሚያሻሽሉ፣ የዜጎችን ጥቅም በማስጠበቅ ላይ ያተኮሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል፤ በተጨማሪም በነዚህ ሂደቶች ውስጥ ከህዝብ ጋር በቂ ምክክርና ውይይት አስቀድሞ መደረግና በተቻለ መጠንም መግባባት ላይ መደረስ ይኖርበታል፣ ይህ ሳይደረግ ቀርቶ ህጎችን፣ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በቀጥታ በህዝብ ላይ መጫን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ሰመጉ ያምናል።

በቅርቡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ‹‹አማካይ የቀን ገቢ ግምት›› በማለት በንግድ ማህበረሰቡ ላይ የጣለውን የግብር መጠን አሳውቋል። ይህንንም ተከትሎ ከንግድ ማህበረሰቡ የገቢ ግምትና የግብር አወሳሰኑ የቀን ገቢያችንን ያገናዘበ አይደለም፣ እጅግ የተጋነነ ነው በማለት ከፍተኛ ቅሬታ በአዲስ አበባ ከተማና በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞችና አካባቢዎች ተሰምቷል፤ ይህ የንግዱ ማህበረሰብ ቅሬታና አቤቱታ የነጋዴዎችን የዜግነትና ሰብዓዊ መብቶችን በአከበረ ሁኔታ ባለመያዙና ባለመፈታቱ፣ ይህ መግለጫ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ፣ የንግድ ሱቆችን መዝጋትና የሥራ ማቆም አድማ ማድረግን ጨምሮ የተለያዩ በርካታ መልኮች ያሉት ከፍተኛ ተቃውሞና አቤቱታ በንግዱ ማሕበረሰብ በኩል በተለያዩ የሐገሪቱ አካባቢዎች መሰማቱ እንደቀጠለ ነው።

በአንዳንድ አካባቢዎች የንግዱ ማህበረሰብ አባላት የሚያነሱትን ቅሬታ እና አቤቱታ ከቅሬታ አቅራቢው የፖለቲካ አመለካከት ጋር በማያያዝ አድሎ እየተፈጸመ እንደሚገኝ አንዳንድ ነጋዴዎች በምሬት ያነሳሉ። እንዲሁም ከ20 እስከ 30 አመታት በንግድ ስራ ተሰማርተው ግብር እየገበሩ የቆዩ ነጋዴዎችም፣ አዲሱ የግብር ጭመራ ላይ ቅሬታቸውን በማሰማታቸው ብቻ፣ ‹‹ለንግድ ስራችሁ መነሻ የሆናችሁን ገንዘብ ከየት አመጣችሁ?›› በማለት እንግልትና መጉላላት እንደተፈጸመባቸው ለሰመጉ ገልጸዋል። የመንግስት አካላት የንግዱን ማህበረሰብ ቅሬታና አቤቱታ፣ የዜግነትና ሰብዓዊ መብቶቻቸውን በጠበቀ አግባብና በትዕግሥት ከማስተናገድና ከመፍታት ይልቅ አቤቱታ በሚያቀርቡ ነጋዴዎች ላይ ዛቻ፣ ማስፈራሪያ፣ ማንገላታት፣ የንግድ ሱቅ ማሸግ፣ የተሸከርካሪ ሠሌዳ መፍታት እና ሕገ ወጥ እስር መፈጸማቸው ሕገመንግሥቱን የሚጻረር መሆኑን ሰመጉ ያምናል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council

የነጋዴው ማሕበረሰብ ተቃውሞውን ለመግለጽ የሚወስዳቸው ሰላማዊ እርምጃዎችም ሆኑ መንግሥት ተቃውሞአቸውን በሰላማዊ መንገድ በሚያሰሙ የንግዱ ማሕበረሰብ አባላት ላይ የሚወስዳቸው ኢሕገመንግሥታዊ እርምጃዎች የመጨረሻ ውጤታቸው ምንም ቢሆን፣ በአጭር ጊዜ ግን የንግዱን ማሕበረሰብ ግለሰብ አባላትና በአጠቃላይ የንግዱንም እንቅስቃሴ እንዲሁም መንግሥትን በልዩ ልዩ መልኩ እንደሚጎዳው ግልጽ ነው፡፡ በተለይም በመብት ጠያቂው የንግዱ ማሕበረሰብ እና መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታን በተሸከመው መንግሥት መካከል የሚወሰዱት ሕጋዊና ሕገወጥ እርምጃዎች ዞሮ ዞሮ እጅግ በሚበዛው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ቀድሞም የነበረውን የሸቀጦችና የአገልግሎቶች እጥረት፣ የዋጋ ንረት፣ የኑሮ ውድነትና የመሳሰሉትን ጫናዎች እያባባሰና የሚያባብስ መሆኑም ሌላው ትኩረት የሚሻ አሳሳቢ ችግር ነው፡፡ ይህም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የዜጎችን የኢኮኖሚና ማሕበራዊ መብቶች የሚጎዳ ስለሆነ መንግሥት ሳይውል ሳይድር ዘላቂና ዕውነተኛ መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል፡፡

የንግዱን ማህበረሰብ እጅግ ያስደነገጠውና ከፍተኛ ቅሬታ የፈጠረበት ‹‹አማካይ የቀን ገቢ ግምት›› ይፋ ከተደረገበት ከሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም. ጀምሮ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) ከተለያዩ የሐገሪቱ አካባቢዎች መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ሲያሰባስብና ቅሬታ ያላቸውን የንግዱን ማህበረሰብ አባላት አቤቱታ ሲቀበል ቆይቷል፡፡ ሰመጉ ዝርዝሩን ከተጨማሪ ጥናት በኋላ ወደፊት ይፋ የሚያደርገው ይሆናል፡፡ ለአሁኑ ግን የጉዳዩን አሳሳቢነት፣ እንዲሁም አፋጣኝ ትኩረትና ዕውነተኛ መፍትሔም የሚሻ መሆኑን ለማሳየት እንዲረዳ ከተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ያነሷቸው ቅሬታዎችና ይህንንም ተከትሎ የተወሰዱባቸው እርምጃዎች ከዚህ በታች በአጭሩና በጥቅሉ ቀርበዋል፡፡

## 1.1 አዲስ አበባ

- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ (መርካቶ) ሰመጉ ያነጋገራቸው በርካታ ባለሱቆች ሐምሌ 2009 ዓ.ም. ይፋ በተደረገው የቀን ገቢ ግብር ትመና ላይ ያላቸውን ቅሬታና ተቃውሞ ለማንጸባረቅ ሐምሌ 17 ቀን 2009 ዓ.ም ሱቃቸውን ዘግተው እንደነበርና የዘጉትን ሱቅ እንዲከፍቱ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠፈባቸው ከዚያም ሱቆቻቸውን ለመክፈት እንደተገደዱ ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡ መንግስት በሚያከራያቸው የንግድ ቤቶች ውስጥ የሚነግዱ ነጋዴዎች ለደቂቃም ቢሆን ሱቆቻቸውን ለተቃውሞ ቢዘጉ የተከራዩትን የንግድ ቤት ለቀው እንዲወጡ እንደሚደረጉ የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 04 ልዩ ቦታው ሲሳይ ሜዳ ገበያ ማዕከል፤ በዚሁ የገበያ ማዕከል ከጀበና ቡና (ቡና ጠጡ) እስከ የችርቻሮ ጥራጥሬ ንግድ የሚሠሩ ነጋዴዎች የዕለት ሽያጭ ግምት ከብር 300-1700 እንደተገመተባቸውና ይህም ማለት "በቀን ከምንሸጠው በ10 እጅ ተባዝቶ ነው የተገመተብን" በማለት ከፍተኛ ቅሬታቸውን ያሰማሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ቂርቆስ የገበያ ማዕከል የሚሠሩ ነጋዴዎች፣ "ተመኑ ገቢያችንን በትክክል ያገናዘበ አይደለም" በሚል ቅሬታ ቢያቀርቡም ‹‹ይጨመርባችኋል›› በማለት የወረዳው የገቢዎች ሀላፊ እንዳስፈራራቸው በምሬት ይገልጻሉ፡፡
- በዚሁ ወረዳ ውስጥ በአንድ የእንጨት ስራ ነጋዴ ላይ በቀን ገቢ ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር / ታስገባለህ ተብሎ ተተምኖበታል፡፡
- ለአጠቃላይ ቀውሱ ተጨማሪ ማሳያ የሚሆነው በአንዳንድ አካባቢዎች የነጋዴዎች ገቢና የተተመነው ግብር ፈጽሞ ተመጣጣኝ አለመሆኑ፣ በተመሳሳይ ንግድ ላይ በተሰማሩ ነጋዴዎች መካከል በጣም የተራራቀ የግብር ተመን መወሰኑና አነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴና ገቢ ያላቸው ነገዴዎች ከፍ ያለ የንግድ እንቅስቃሴና ገበያ ካላቸው ነጋዴዎች እኩል የግብር ተመን የተጣለባቸው መሆኑ ነው፡፡

## 1.2 ልዩ ልዩ የሐገሪቱ አካባቢዎች፡ የግብር ይስተካከልን ጥያቄያቸውን ጎላ ባለ መልኩ ነገር ግን በሰላማዊ መንገድ ከጠየቁት መካከል የሚከተሉት አካባቢዎች ነጋዴዎች ይገኙበታል፤

- **አማራ ክልል**: ባህርዳር፣ ደብረታቦር፣ ወልድያ፣ ደሴ፣ ሸዋሮቢት፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ደንበጫ፣ ፍኖተሰላም፣ ሞጣ እና በተለያዩ ከተሞች፣
- **ኦሮሚያ ክልል**: አምቦ፣ ጀልዱ፣ ጊንጪ፣ ግንደበረት፣ ሆለታ፣ ባኮ፣ ጉደር፣ ጃጂ፣ ደንቢ ዶሎ፣ ጊምቢ፣ መንዲ እና ነቀምት፣
- **ደቡብ ክልል** : ሀዋሳ፣ ወላይታ ዘንገሱባ ከተማ፣ አርባ ምንጭ፣ ጎፋ፣ ሳውላና አካባቢው፣



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

- **ምስራቅ ኢትዮጵያ፡** አዲሱን የግብር ተመን በተመለከተ ቅሬታ በስፋት ከሚታይባቸው አካባቢዎች መካከል ደደር፣ ጨለለንቆ፣ አሰበ ተፈሪ፣ ጭሮ፣ በዲሳ፣ ገለምሶ፣ መቻራ፣ ቆቦ፣ ሐረር፣ ሀሮምያ፣ አወዳይ፣ ጂግጂጋ፣ ድሬደዋ፣
- **አዲስ አበባ ከተማ፡** ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ሽሮሜዳ፣ ኮልፌቀራኒዮ ክ/ከተማ፣ መርካቶ፣ ሃያሁለት፣ ባሌ ቡልቡላ፣ አራዳ ክ/ከተማና በሌሎችም ክ/ከተሞች ቅሬታዎች ቀርበዋል፡፡

ከሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በተወሰደው ‹‹አማካይ የቀን ገቢ ግምት›› መነሻነት የእለት ገቢያቸውን ያላገናዘበ ግብር የተጣለባቸው የንግዱ ማሕበረሰብ አባላት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ድርጅታቸውን በመዝጋትም ሆነ ሳይዘጉ በሰላማዊ መንገድ እንዲስተካከልላቸው ጥያቄና አቤቱታ ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡ ቅሬታውና አቤቱታው በአጠቃላይ በሀገሪቱ በሚገኙ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ዘንድ ታይቷል፡፡ የነጋዴው ማሕበረሰብ ቅሬታዎችም በተለያዩ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን እንደቀረቡና በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹40 በመቶ የሚሆነው የግብር ግምት ስህተት ነበር›› በማለት በመገናኛ ብዙሐን መግለጻቸው ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የንግዱ ማሕበረሰብ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ለአንዳንድ ተመልካቾች መልስ ያገኙ ቢመስሉም እንዲሁም መንግሥት ለአብዛኞቹ ቅሬታዎች በቅሬታ መስማት ሥርዓት መፍትሔ ሰጥቻለሁ ቢልም፣ ሰመጉ ያሉት መረጃዎች የሚያመለክቱት ግን ጉዳዩ ገና እልባት አለማግኘቱን ነው፡፡ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያና በአማራ እንዲሁም በሌሎች የሐገሪቱ አካባቢዎች በርካታ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች በተጣለባቸው ወይም ተሻሽሎላቸዋል በተባለው የግብር ተመን ላይ አሁንም ቅሬታ ስላላቸው ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ አንዳንዶች አቤቱታችን በየደረጃው በሚገኙ የመስተዳድር እርከኖች ምላሽ አላገኘም በሚል ወደፍርድ ቤት እየሄዱ ነው፡፡ ሌሎች ጥቂት የማይባሉ ደግሞ የቀራቸው አማራጭ የንግድ ፈቃዳቸውን መመለስ ብቻ መሆኑን እየገለጹ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው የንግዱ ማኅበረሰብ ችግር ገና ያልተፈታ መሆኑንና ጥያቄውን ኃላፊነትና አስተዋይነት በተሞላበት መንገድ አሁንም ሳይረፍድ መፍታት እንደሚገባ ነው፡፡

መንግሥት ይህን ከፍተኛ የግብር ጭማሪ በነጋዴው ላይ የጣለው፣ ምናልባት ወጪውን ለመሸፈን የሚረዳ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት እንደሆነ አድርጎ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላም በኩል የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ የንግዱ ህብረተሰብ ፍትሀዊ፣ ከአድሎ ነጻ የሆነ፣ አቅምን ያገናዘበ እንዲሁም በመተማመንና በተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ ግብር መክፈል እንዳለበት እምነቱ ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ነገር ግን መንግስት የንግዱን ማሕበረሰብ ጥያቄ በሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ መስጠት ይገባዋል፡፡ የንግድ ድርጅቶችን በማሸግ፣ ነጋዴዎችን በማስፈራራትና ያለአግባብ በማሰር እየወሰደ ያለውን ህገወጥ ድርጊት እንደገና በፍጥነት ሊያጤንና ሊያርምም ይገባል፡፡ ከእልህና ጥድፊያ ይልቅ በትዕግሥትና በእውነተኛነት ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት ፍትሃዊና አቅምን ያገናዘበ እንዲሁም ነጋዴውንም ሆነ መላ ሕዝቡን ዋና ተጠቃሚ የሚያደርግ ግብር እንዲጥልና እንዲሰበስብ እንዲሁም ሁሉንም የንግድ ማሕበረሰብ አባላት ያለአድልዎ በእኩልነት እንዲያስተናግድ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም መብታቸውን በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ በመጠየቃቸው ምክንያት የታሰሩ ነጋዴዎች እንዲፈቱ፣ የታሸጉባቸው ሱቆች እንዲከፈቱና ማስፈራራትና ማዋከቡም እንዲቆም ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

## 2. በድንበር ይገባኛል ጥያቄዎች ሰበብ የከፉ ግጭቶች ከመቀስቀሳቸው በፊት መንግስት ከሕብረተሰቡ ጋር በመመካከር አስቸኳይ መፍትሄ ይስጥ

ሰመጉ በሰበሰባቸው የተለያዩ መረጃዎች መሰረት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አካባቢዎች ከማንነት፣ ከአስተዳደርና ከድንበር ይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ግጭት እየተቀሰቀሰ ነው፣ ወይም ውሎ አድሮ ሊቀሰቀስ ይችላል፡፡ ከእነዚህም ግጭቶች አንዳንዶቹ ቀድሞውንም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ቀውሶች አስከትለዋል፤ በጊዜ ካልተፈቱም ስፋቱንና መዳረሻውን ለመተንበይ የሚያስቸግር የከፋ የሰብዓዊ መብቶች እንዲሁም የሰላም መረጋጋትና የባሱ የአንድነት ቀውሶችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የሰመጉ ስጋት ነው፡፡

2.1 **የኦሮሚያና የሶማሌ ክልሎች የድንበር ማካለል፡** እነዚህ ሁለት ክልሎች የድንበር ስምምነት ሰነድ የተፈራረሙ ቢሆኑም በአንዱ ክልል ውስጥ ይተዳደሩ የነበሩ ቀበሌዎች ወደ ሌላኛው እንዲተዳደሩ በመወሰኑ በሁለቱም ማሕበረሰቦች ዘንድ ቅሬታ ፈጥሯል፤ እስካሁንም አልተፈታም፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚችለውን ግጭት

ሊያስቀር አልቻለም፡፡ በነሐሴ ወር 2009 ዓ.ም. አጋማሽና መጨረሻ እንዲሁም ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ በሚዘጋጅበት ወቅትም በተፈጠሩትና እየተፈጠሩ ባሉት የክልሎቹ ድንበር ግጭቶች ምክንያት ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሕይወት እየጠፋ ነው፣ በርካታ ዜጎች ቆስለዋል፣ በልዩ ልዩ መልክ እየተጎዱም ነው፡፡ በተለይም በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሚኤሶ ወረዳ እንዲሁም የባሌና የቦረና አዋሳኝ በሆነው የምሥራቅ ሐረርጌ ባቢሌ እና ፊቅ ወረዳዎች፣ በሀዊ ጉደና ወረዳ ግጭት እየተካሄደ ነው፡፡ በተጨማሪም የግጭት አደጋ ካንዣበበባቸው አካባቢዎች መካከል የጉርሱም ወረዳ፣ ቦርደዴ (ሀርደም ቀበሌ) እና ቦረና ወረዳዎች ይገኙበታል፡፡

2.2 **በቤኒሻንጉል ጉሙዝና ኦሮሚያ ክልሎች፡** በድንበር ውዝግብ ምክንያት ሰርቦ፣ አባያና ደንቢ በሚባሉ አካባቢዎች በሚኖሩ የኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት ላይ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰባቸው ይገኛል፤ በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ በመፈናቀል ላይ እንደሚገኙ ሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

2.3 በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሚኖርበት ገላና፣ አባያና የቡሌ ሆራ ወረዳዎች አዋሳኝ አካባቢዎችና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የኮሬ ብሄረሰብ በሚኖርበት በአማሮ ወረዳ ድንበሮቹን እንደ አዲስ ለመለየትና ለማካለል በተደረገው እንቅስቃሴ በሁለቱ ወንድማማች ማሕበረሰቦች መካከል ግጭት ተደጋጋሚ ግጭት ተቀስቅሶ የብዙ ዜጎች ህይወት ጠፍቷል፣ ከፍተኛ ንብረትም ወድሟል፡፡

2.4 በደቡብ ብሔር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ በሲዳማ ዞን በቦረቻ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የሲዳማ ብሔረሰብ አባላትና በወላይታ ዞን በምዕራብ አባያ ሁንቦ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የወላይታ ብሔረሰብ አባላት መካከል የተሞከረውን የድንበር ማካለል ሂደት ተከትሎ የሚታየው የድንበር ይገባኛል ውጥረት አስከፊ መዘዝና የሰብዓዊ መብቶች ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ሰመጉ ያምናል፡፡

## 3. ማሳሰቢያ

አስደንጋጭ የሆነውና በበቂ ሁኔታና ሙያ ያልተጠናው የግብር አወሳሰን በርካታ የንግዱን ማህበረሰብ አባላት ቅር ያሰኘና በአንዳንድ አካባቢዎች ቁጣን የቀሰቀሰም ሆኗል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ግብሩ በተጠናና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ባለመተመኑና በበቂ ሁኔታ ከህብረተሰቡ ጋር ምክክር ባለመደረጉም ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት ቅሬታ ያነሱ ነጋዴዎችን አቤቱታ በመስማት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥና የግብር አወሳሰኑም በድጋሚ እንዲያጤን ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ከማንነት፣ ከአስተዳደርና ከድንበር ይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ግጭት መቀስቀሱን፣ እየተቀሰቀሰ መሆኑን ወይም ሊቀሰቀስ እንደሚችል ሰመጉ የሰበሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተመሳሳይ አካባቢዎች ከዚህ በፊት ተደጋጋሚ ግጭቶች መከሰታቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የተፈሩት ግጭቶች በድጋሚ ተቀስቅሰው የሰው ህይወትና ንብረት ከመጥፋቱና በቀላሉ የማይሽር ጠባሳም ከመፈጠሩ በፊት መንግስት የፖሊሲዎቹን፣ የሕግና የአሰራሮቹን እንዲሁም የአፈጻጸሞቹን ትክክለኛነትና አዋጭነት እንደገና መርምሮ፣ ከሚመለከታቸው ማሕበረሰቦችም ጋር በግልጽ፣ በቅንነትና የጋራ ጥቅምንና ደህንነትን ማዕከል ባደረገ መንፈስ በመወያየት በአስቸኳይ ዘላቂና የማያዳግም መፍትሄ እንዲሰጥ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል እና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡